# ማኅበር ተጋሩ ሰሜን ኣሜሪካ (ማ.ተ.ሰ.ኣ)
# UNION OF TIGREANS IN NORTH AMERICA (UTNA)

P.O.BOX 73736
Washington, DC 20056
utnaoffice@gmail.com

Tel. (202) 749-8609
Fax. (202) 265-8703
www.utna.org


ሜይ 27፣ 2020
ዋሽንግተን ዲሲ

### በወቅታዊ ጉዳይ ከትግራይ ተወላጆች ማሕበር በሰሜን ኣሜሪካ የተሰጠ መግለጫ

የትግራይ ህዝብ በተደጋጋሚ ከህደት ሲፈጸምበት ሁሉንም ችሎ ነገ የተሻለ ቀን ይሆናል በማለት በትእግስት፣ በአስተዋይነት እና አርቆ በማሰብ የተለያዩ ችግሮች ሲደርስበት አሁንም ሁሉ ተቋቁሙ ለሰላም ያለው ቁርጠኝነት በተደጋጋሚ በተግባር አሳይቷል። በተለይ ባለፉት ሁለት ዓመታት በተደጋጋሚ የፌዴራል መንግስት ትግራይ ላይ ተፅእኖ በማድረግ የትግራይን ህዝብ ለማንበርከክ ያልፈነቀለው ድንጋይ የለም። ይህ አላንስ ብሎ የተሻለ ሰላም እና መረጋጋት የሚታይበት ክልል ምቀኝነት በሚመስል መልኩ አሁን ሐሰተኛ ወሬ በማሰራጨት ለማበጣበጥ የሚደረግ ሙከራ ታክሎበታል። የፌዴራል መንግስት ከዚህ ተግባር ራሱን እንዲቆጥብ ማሕበራችን ይጠይቃል። ይህ ድርጊት አገራችን ኢትዮጵያ ወደ ከፋ የመጨረሻ ምእራፍ እየገባች መሆኑን ያመለክታል። በጣም አሳዛኝና በአንድ አገር በመንግስት ሚዲያዎች የተቀነባበረ ውሸት በሬ ወለደ በትግራይ ክልል ከፍተኛ ችግር እንደተፈጠረ ውጥረት እንዳለ አስመስሎ የራሱን ህዝብ ማሸበር ከአንድ መንግስት ያላት አገር በፍጹም የማይጠበቅ በጣም የወረደ ድርጊት ነው። ይህ በተቀነባበረ እና ሴራ በሚመስል መልኩ የውጭ ሀይል ጣልቃ ታክሎበት ሰለማዊ የህዝባችን ኑሮ ለማበጣበጥ ሲሰራበት የቆየ ተግባር ማሕበራችን ብጽኑ ያወግዛል።
ይህንን ድራማ የያቀነባበሩ እና በድራማው የተሳተፉ አካላት ሁሉ በሕግ እንዲጠየቁ ማሕበራችን ጥሪውን ያቀርባል።

የትግራይ ተወላጆች ማሕበር በሰሜን አሜሪካ
ዋሽንግተን ዲሲ